«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ
ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ
ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ
ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ
ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3÷16-17



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)÷130

Global Good News Literature
የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
P.O.BOX 451336
Los Angeles, CA 90045
email: info@globalgoodnews.org
Copyright © 2008



## ማውጫ

ክፍል ፩

| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት ዐሥራ ሁለት፡- አገልግሎት | 5 |
| ፩. የአገልግሎት ጥሪ | 5 |
| ፪. የአገልግሎት መሠረት | 5 |
| ፫. የአገልግሎት ዐላማ | 5 |
| ፬. የአገልግሎት አቀባበል | 6 |
| ፭. የአገልግሎት ምንጭ | 7 |
| ፮. የአገልግሎት አሠራር | 7 |
| ፯. የአገልግሎት ዕንቅፋቶች | 10 |
| ትምህርት ዐሥራ ሁለት፡- አገልግሎት - ጥያቄዎች | 12 |

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው። «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው። ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን።

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል። ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ።

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል። አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው። ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን።

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን።





# ክፍል ፩



**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»**
**መዝ. 118(119)፥130**

# ትምህርት ዐሥራ ሁለት፡- አገልግሎት

## ፩. የአገልግሎት ጥሪ

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁለት ዐይነት ጥሪ አለው:: የመጀመሪያው ጥሪ ለደኅንነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለአገልግሎት ነው:: በማቴ. 11÷28፣ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ:: ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና::» በማለት ሁለቱንም ዐይነት ጥሪ ለሰዎች ሲያቀርብ እናነባለን:: የመጀመሪያው የደኅንነት ጥሪ ከኀጢአትና ከኑሮ ሸክም ለማረፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው የአገልግሎት ጥሪ ደግሞ የጌታን ልዝብ (ዐንገት የማይከረክር) ቀንበር ለመሸከም ነው:: በእነዚህ ሁለት ጥሪዎች መካከል ከጌታ የምንማርበትና በተለይ ለሁለተኛው ጥሪ የምንዘጋጅበት ዘመን አለ (ከእኔ ተማሩ)::

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ከእርሱ ጋር እንዲኖሩና እንዲያገለግሉ ጠራቸው:: «ወደ ተራራም ወጣ፤ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፤ ወደ እርሱም ሄዱ:: <u>ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና</u> ለመስበክ እንዲልካቸው፣ ድውዮችንም ሊፈውሱ፣ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለት አደረገ» (ማር. 3÷13-15)::

ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ክፍሎች የምንረዳው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ሲጠራን፣ በመጀመሪያ ከእርሱ ጋር እንድንኖርና ከእርሱ እንድንማር፣ ከዚያም እርሱን እንድናገለግለው እንደ ጠራን ነው:: በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ሲያወጣ ፈርዖንን፣ «ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ» (ዘፍ. 7÷16) ነበር ያለው::

## ፪. የአገልግሎት መሠረት

የአገልግሎት ሁሉ መሠረት ራስን ለእግዚአብሔር መቀደስ ነው:: «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ! ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሐር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው::» (ሮሜ 12÷1)

«ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ ማን ነው?» (1ዜና 29÷5)

## ፫. የአገልግሎት ዐላማ

በቤተ ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት ይሰጣል:: ይሁን እንጂ የማንኛውም አገልግሎት የመጨረሻ ግብ ሁለት ነው::





### 1. <u>ማስታረቅ</u>

የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት በአዳም በደል ምክንያት ከአምላኩ ጋር የተጣላውን ሰው ማስታረቅ ነው:: «ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን፣ <u>የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን</u> ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፣ በደላቸውንም አይቈጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ:: እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ፣ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን::» (2ቆሮ. 5÷18-20)

ይህ አገልግሎት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅ የሚያደርግ የቃልና የምልጃ አገልግሎት ነው::

### 2. <u>ማሳደግ</u>

በክርስቶስ በማመን የተደረገው ዕርቅ ሥር እንዲሰድና ወደ ጽኑ ኅብረት እንዲደርስ የማድረግ ኀላፊነት ነው:: የእውነተኛው ኅብረት መለኪያም የታረቀው ሰው ክርስቶስ ኢየሱስን መምሰሉ ነው:: እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን ካደለበት ምክንያት አንዱ «....የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርሰን፣ ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ እንደ ሆነው፣ እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው::» (ኤፌ. 4÷13) ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ግብ ሲናገር፣ «በጥበብ ሁሉ ማናቸውንም ሰው እየመከርንና እያስተማርን እያንዳንዱ በክርስቶስ ሙሉ ሰው እንዲሆን በማድረግ ክርስቶስን እናሳውቃለን» (ቈላ. 1÷28)ይላል::

## ፬. የአገልግሎት አቀባበል

ደኅንነትን በጸጋ እንደ ተቀበልን ሁሉ፣ አገልግሎትንም በጸጋ እንቀበላለን:: ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን በራሱ ጽድቅና ኀይል ለማገልገል አይችልም:: ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ነውር የሌለብንና ያለ ኀጢአት እንደ ነበርን አድርጎ እንደ ተቀበለን ሁሉ፣ እንዲሁ አገልግሎትንም በክርስቶስ የሚገባን አድርጎ ስለ ቈጠረን ይሰጠናል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን በማስመልከት ስለ አገልግሎቱ ሲናገር፣ «እግዚአብሔር በምሕረቱ ይህን አገልግሎት ስለ ሰጠን፣ ተስፋ አንቈርጥም» (2ቆሮ. 4÷1)፤ «ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቈጠረኝ ኀይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ» (1ጢሞ. 1÷12) ይላል:: አገልጋይ የሆነ ሁሉ ሊገነዘበው የሚገባ ነገር፣ አገልግሎትን የተቀበልነው መልካም ሰዎች ስለ ሆንን ወይም ችሎታችን ታይቶ ብቃት እንዳለን ተረጋግጦ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እንዲሁ በምሕረቱ የሰጠን መሆኑን ነው::

«ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ... ራሳችን የበቃን አይደለንም::» (2ቆሮ. 3÷5)

## ፭. <u>የአገልግሎት ምንጭ</u>

የአገልግሎት ሁሉ ምንጭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጠን ሰው ይመስለናል፤ ነገር ግን እውነተኛ አገልግሎት ሁሉ የሚመጣው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በእግዚአብሔር ሰዎች ወይም በቤተ ክርስቲያን በኩል ሊመጣ ይችላል፤ ምንጩ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

ጳውሎስ ስለ ነበረው አገልግሎት እንዲህ ይላል፤ «ነገር ግን ሩጫዬንና <u>ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት፣</u> እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቈጥራለሁ::» (ሐዋ. 20÷24)

ይህ ምስጢር፣ ማለትም አገልግሎት ሁሉ ከጌታ ብቻ እንደ ሆነ የገባው ሰው፣ «አገልግሎት ለምን አልተሰጠኝም?» ብሎ አያጕረመርምም፤ ምክንያቱም አገልግሎትን የሚጠብቀው ከሰው ሳይሆን ከጌታ ነው::

ከጌታ አገልግሎትን መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ከተቀበልንም በኋላ እያንዳንዷን ርምጃ ያለ እርሱ ርዳታ መሄድ አንችልም፤ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም::» (ዮሐ. 15÷5)

በእርሱ ርዳታ ግን ሁሉን እንችላለን፤ «ኀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ::» (ፊል. 4÷13)

## ፮. <u>የአገልግሎት አሠራር</u>

በመሠረቱ በአገልግሎት መሰማራት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ለመንግሥቱ ሥራ ዐብሮ መሰለፍ ማለት ነው፤ «ከእርሱ ጋር ዐብረን የምንሠራ ነንና» (1ቆሮ. 3÷9)፤ በተጨማሪም በዮሐ. 15÷5፣ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ብሎናል:: ይህም ስለ ሆነ የሥራው ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ከሠራተኛው የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉት ማለት ነው:: እግዚአብሔር አገልግሎቱ እንዲሰጥ የሚፈልገው:-

1. **<u>በዳግም ልደት:-</u>** የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት የመንፈስ አገልግሎት ስለ ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለመስጠት ከመንፈስ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋል:: ዳግመኛ ሳይወለድ ማለትም መሠረታዊውን ዕርቅ ከእግዚአብሔር ጋራ ሳያደርግ፣ አገልግሎት ለመስጠት የሚሞክር ሰው እያገለገለ ያለው የእግዚአብሔርን ሐሳብ ሳይሆን፣ የራሱን ምኞትና ሐሳብ ነው::

2. **<u>በጸሎትና በቃሉ በመመራት</u>:-** በጸሎትና በቃሉ ያልተደገፈ አገልግሎት ሁሉ በገለባና በአገዳ (በእሳት ተፈትኖ በማይወጣ ነገር) እንደ መሥራት ይቈጠራል (1ቆሮ. 3÷12-15):: የሐዋርያት አገልግሎት በጸሎትና በቃሉ የተመሠረተ እንደ ነበረ እናነባለን፤ «እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን» (ሐዋ. 6÷4) አሉ::





ለአገልግሎት <u>በመንፈስም በአእምሮም</u> መዘጋጀት ያስፈልጋል:: ጸሎት መንፈሳችንን ያዘጋጃል፤ ቃሉ ደግሞ አእምሮአችንን ያዘጋጃል::

3. **<u>በመንፈስ ቅዱስ ድጋፍ:-</u>** ያለ መንፈስ ቅዱስ ድጋፍ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አገልግሎት መስጠት አንችልም፤ «በመንፈሴ እንጂ በኀይልና በብርታት አይደለም::» (ዘካ. 4÷6) የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን አገልግሎት እንደ ሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል፤ «እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለዐዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል::» (2ቆሮ. 3÷6)

4. **<u>በአክብሮት</u>:-** ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ብሉይ ኪዳን አገልግሎት ሲናገር፣ ያ ይሻር የነበረው፣ ቋሚነት ያልነበረው እንኳ በክብር ይደረግ እንደ ነበረ አስገንዝቦ፣ ይልቁንስ ይህ የማይሻረው የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት አብልጦ በክብር መሆን እንዳለበት ያስረዳል (2ቆሮ. 3÷7-11):: የብሉይ ኪዳን አገልጋዮች ከማገልገላቸው በፊት ራሳቸውን ከኀጢአትና፤ ከእድፍ ያነጻሉ፤ የተለየ የክህነት ልብስ ይለብሳሉ፤ የተቀደሰና ንጹሕ የሆነ መሥዋዕት ይዘው ለአገልግሎት ይቀርባሉ:: ካህናቱ ወደ መገናኛው ድንኳን የሚገቡት እንዲሁ ተራ እንደ ደረሳቸው አልነበረም:: ያ ይሻር የነበረ፤ የሞትና የኵነኔ አገልግሎት እንደዚህ በጥንቃቄ ይደረግ ከነበረ፣ ያሁኑ በክርስቶስ የሆነው አገልግሎት በበለጠ ክብር፣ በጥንቃቄ፣ በአክብሮትና በፈሪሀ እግዚአብሔር ሊከናወን ይገባል::

5. **<u>የሚያሳፍረውን ስውር ነገር በመጣል</u>:-** በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑ ሰዎችም እንኳ ቢሆኑ የሚያሳፍርን ስውር ነገር ይዘው እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበት ጊዜ አለ:: ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ሲናገር፣ «ነገር ግን የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና በተንኰል አንመላለስም፤ የእግዚአብሔርን ቃል በውሸት አንቀላቅልም...» (2ቆሮ. 4÷2) ይላል:: የሚያሳፍረው ስውር ነገር፣ ስውርነቱ ለሰው እንጂ ለሥራው ባለቤት ለእግዚአብሔር አይደለም:: በሰው ፊት ምስጋናን እየተቀበልን ሥራችንን በሚመዝንና ፍሬያችንን በሚሰጥ እግዚአብሔር ፊት ዋጋ ቢስ ከሆንን ምን ይረባናል? እግዚአብሔር ከትዕግሥቱ የተነሣ የሰወርነውን እያየ ዝም ሲለን፣ ከልባችን መደንደን የተነሣ ከእኛ ጋር የተባበረ ወይንም የምናደርገውን ያጸደቀ ይመስለን ይሆናል:: ለጊዜው ዝም ቢልም፣ እግዚአብሔር ነገርን ወደ አደባባይ የሚያወጣበት ቀን ይመጣል:: በመዝሙረ ዳዊት፤ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገሩ፣ ተስፋውን ወይም ቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽምላቸው አድርገው የሚያወሩ፣ ነገር ግን በቃሉ የማይኖሩ ሰዎች ያደረጉትን ከዘረዘረ በኋላ፣ «... ይህን ስታደርግ ዝም በማለቴ እኔም እንደ አንተ የሆንሁ መሰለህን? አሁን ግን ፊት ለፊት ነገሩን ገልጬ እገሥጽሃለሁ::» (መዝ. 50÷21) የሚለውን በዐዲሱ ትርጒም እናነባለን::

6. **<u>መሸቃቀጥ በሌለበት መንገድ</u>:-** ጳውሎስ በዘመኑ ወንጌልን የሚሸቃቅጡ ሰዎች እንደ ነበሩ ይናገራል:: ምንም እንኳ እንደዚህ ዐይነት ሰዎች

ቢኖሩም፣ እርሱ ግን እንደ እነርሱ እንዳላደረገ ይገልጻል:: «የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎች አይደለንምና» (2ቆሮ. 2÷17) ካለ በኋላ እውነትን በመግለጥ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት በጎ ኅሊና እንደ ነበረው አስረድቷል (2ቆሮ. 4÷2)::

7. **<u>ራስን ባለመስበክ:-</u>** የአገልግሎት ተጠሪነቱ ለክርስቶስ እንጂ ለራሱ አይደለም:: ራሱን ለማስተዋወቅ የሚሞክር አገልጋይ ተልእኮውን የዘነጋ ነው:: ክርስቶስን መስበክ፣ የክርስቶስንም ሥራ ለዓለም ማወጅ እንጂ መልእክተኛው መልእክት መሆን ሲጀምር ወንጌል ይበረዛል፤ መልእክቱም ተለውጦ፣ በትክክለኛው መልእክት ፈንታ የተሳሳተ ዐላማ እንኳ ፈጽሞ /motive/ ሲሰበክ፣ የወንጌልን ጣዕም ይለውጠዋል::

8. **<u>ሌሎችን ለመጥቀም በማሰብ:-</u>** አገልግሎት ኀላፊነት ነው:: ይሁን እንጂ ኀላፊነቱን የምንወጣው በፍቅር ሊሆን ይገባል:: የግብር ይውጣና የአገልግሎትን ሱስ ለመወጣት ሲባል ብናገለግል፣ ጥቅም የሚያገኙት ሰዎች ብዙ አይሆኑም::» «እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ::» (ፊል. 2÷4)

9. **<u>መከራን ለመቀበል በመዘጋጀት:-</u>** የወንጌል አገልግሎት ሰዎችን ሁሉ ደስ የምናሰኝበት ወይም በሁሉ ፊት ሞገስ የምናገኝበት አገልግሎት አይደለም:: በውስጥም ሆነ በውጭ መከራ የሚመጣበት ጊዜ አለ:: በዚህ ሁሉ ግን መከራን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አስፈላጊ ነው:: «እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፣ አብረኸኝ መከራ ተቀበል::» (2ጢሞ. 2÷3)

10. **<u>በቅንነት:-</u>** በቅንነት የሚሄዱ የእግዚአብሔርን ሐሳብ መረዳት ይችላሉ፤ «ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና» (ማቴ. 5÷8)፤ «<u>በቀና መንገድ የሚሄድ</u> እርሱ ያገለግለኛል::» (መዝ. 101÷6):: በአገልግሎታችን ልናስብ የሚገባን ምንም <u>እንኳ ስለምናገለግለው ሰው ቢሆንምና በሰዎች ፊት ብንቆምም</u>፣ በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንደሆንን ልናስብ ይገባናል:: ይህ ግንዛቤ ያለው ሰው እግዚአብሔርን በቅንነት ማገልገል ይችላል:: ሐዋርያው፣ «... <u>በቅንነት</u> ግን ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን» (2ቆሮ. 2÷17) ይላል:: እርሱ በግልጽ የተረዳው ጉዳይ አለ:: በሚያገለግልበት ጊዜ መልእክቱ በትክክል መድረሱን በሚመዝን፣ ለታማኝነት ዋጋን በሚሰጥ አምላክ ፊት መሆኑን እንዲሁም ብቃትንና ኀይልን በሚሰጥ ጌታ ውስጥ መሆኑን ያውቃል:: ይህ ዐይነቱ አገልግሎት የእግዚአብሔር ማኅተም ያለበት አገልግሎት ነው:: እንግዲህ አገልጋዮች የሆንን ሁላችን የሥራው ባለቤት ሳያቋርጥ ከእኛ ጋር እንዲሆንና ሥራችንንም እንዲያጸድቅልን ከፈለግን፣ የእርሱን ሐሳብ እርሱ በሚወደው መንገድ ማገልገል ይገባናል::





11. **<u>በኅብረት:-</u>** አገልግሎት ከሰው ጋር ዐብሮ መሥራትንና ዐብሮ መሠራትን ያጠቃልላል:: «... በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ ዐብራችሁ ትሠራላችሁ::» (ኤፌ. 2÷22) አገልግሎቱ የኅብረት አገልግሎት ነው፤ መተያየት፣ መሰብሰብ፣ መመካከር፣ መጠባበቅ፣ የሚያስፈልገው አገልግሎት ነው:: ይህ ሆኖ እያለ ግን አብዛኛውን ጊዜ ዐብሮ መሥራትም ሆነ መሠራት ቀላል ሆኖ አናይም::

12. **<u>በትሕትና:-</u>** ያለ ትሕትና እውነተኛ አገልግሎት መስጠት አንችልም:: ክርስቶስ የትሕትናን አገልግሎት ሊያስተምረን ፈልጎ፣ ዝቅ በማለት የደቀ መዛሙርትን እግር አጠበ:: ካጠበ በኋላም፣ «ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን?..» (ዮሐ. 13÷13) በማለት ዝቅ ብለን እንድናገለግል ምሳሌ ተወልን::

## ፯. <u>የአገልግሎት ዕንቅፋቶች</u>

የአገልግሎትን መሥመር ሽካራ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ ዋናዎቹ:-

1. የአገልግሎትን ዐላማ አለማስተዋል፣
2. የአገልግሎትን ምንነት አለመረዳት፣
3. የአገልግሎትን አፈጻጸም አለማወቅ::

በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ጥሩ መረዳት ከሌለ፣ በአገልግሎት ብዙ መዛባትና መዛነፍ ይመጣል:: በአንድ ልብ፣ በአንድ ሐሳብና በአንድ ፍቅር ማገልገል አሰቸጋሪ ይሆናል:: እግዚአብሔር ልጆቹን በክርስቶስ በማመንና እርሱን በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት እንድንደርስ ጠርቶናል፤ የአገልግሎታችን ልዩነትም እንኳ አንድነትን የሚያመጣ ነው:: ይህ አንድነት እንዳይኖር፣ በአንዱ ጸጋ ሌላው እንዳይገለገልም ትልቅ ምክንያት የሚሆነው የትሕትና አለመኖር ነው::

በፊልጵስዩስ 2÷1-4 በተጻፈው መሠረት:-

<u>ትሕትና በሌለበት አገልግሎት የሚታዩ ገጽታዎች</u>

1. እኔ እበልጣለሁ፤ የእኔ አሠራር ብቻ ልክ ነው... ወዘተ ባይነት፣

2. ወገናዊነት (የቡድን ስሜት) በአሠራር ሁሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚበጀውን ሳይሆን፣ የቡድኑን ስም የሚያስጠራና ቡድኑን የሚጠቅም ነገር ብቻ ለማድረግ መጣር፣

3. የራስን ጥቅም ወይም ከንቱ ረብን መፈለግ፤ ዝናንና ታዋቂነትን ለማትረፍ ጥረት ማድረግና ከንቱ ውዳሴን መሻት::

**<u>ትሕትና በሌለበት አገልግሎት፡-</u>**

ሀ. የመንፈስ ኅብረትና የመንፈስ መፈታት አይኖርም።

ለ. አገልግሎቱ ቃል ብቻ የሆነ ፍሬ የሌለው ሩጫ ይሆናል።

ሐ. ሌሎችም ሆኑ ራሱ አገልጋዩ አይታነጹበትም።

መ. እውነተኛ እድገት የሌለው ሕይወት ይሆንና እንደ ቆመ ውሃ ለምንም የማይጠቅም፣ መጥፎ (ሽታ) ያለው አገልግሎት ይሆናል።

**<u>በትሕትና በሚከናወን አገልግሎት፡-</u>**

ሀ. አንዱ ሌላውን ከራሱ እንደሚሻል አድርጎ መቍጠር ይኖራል።

ለ. የጸጋ መከባበር ይኖራል።

ሐ. ሌላውን ለመጥቀም የራስን ጥቅም (መብት) መተው ይኖራል።

«ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።» (1ጴጥ. 5÷5)

**ትሕትናን እንደ ልብስ በመልበስ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ፣ ሌሎችን የሚያንጽና እራሳችንን የሚገነባ አገልግሎት እንድንሰጥ ጌታ አምላካችን ይርዳን።**





## ትምህርት ዐሥራ ሁለት፡- አገልግሎት

የመታወቂያ ቍጥር፤ ____________________
ስም፣ ____________________
አድራሻ፣ ____________________
____________________
____________________

1. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚያቀርባቸው ሁለት ጥሪዎች ምን ምን ናቸው? ልዩነታቸውስ ምንድን ነው?

2. የአገልግሎት ሁሉ ሁለት ዐበይት ዐላማዎች ምንድን ናቸው? ለእያንዳንዱ ዐጭር ማብራሪያ ስጥ።

3. የአገልግሎት ሁሉ መሠረት ምንድን ነው? ምንጩስ ማን ነው?

4. አገልግሎት እንዴት ባለ ሁኔታ መሰጠት አለበት? ከዘረዘርሃቸው ውስጥ ሦስቱን አብራራ።

5. በፊልጵስዩስ 2÷1-11 በተዘረዘረው መሠረት አገልግሎት ፍጹም እንዳይሆን የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

6. ትሕትና ባለበትና ትሕትና በጐደለው አገልግሎት መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ።

**አገልግሎትህን ስትመዝነው እንዴት ሆኖ አገኘኸው? ትክክለኛ የአገልግሎት ፈለግን እየተከተልህ ካልሆነ፣ ምን ማድረግ አለብህ?**